# ወርሃዊ የአየር ጠባይ

# ግምገማና እና ትንበያ መጽሔት

## ከሜይ 1-31/2022 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ እንዲሁም

## ከጁን 1-30/2022 የሚኖረው የአየር ጠባይ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ሜይ 2022
አዲስ አበባ

| ርዕስ | ገፅ |
|---|---|


እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2022 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ ...... 3

ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ...... 4

ካርታ 7 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት ...... 5

ካርታ 8 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ...... 6

ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ...... 6

እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2022 የነበረው የአየር ጠባይ በእርሻ ...... 7

ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ...... 7

ካርታ 9 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ...... 7

እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2022 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ...... 8

ካርታ 10 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ...... 8

እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2022 የሚኖረው የአየር ...... 9

ጠባይ አዝማሚያ ...... 9

እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2022 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ...... 10

እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2022 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በውሀው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ...... 11


# እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2022 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

ባለፈዉ የሜይ ወር ለደመና መፈጠር አመቺ ሁኔታን የሚፈጥሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ እና በምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተሻለ ገፅታ ነበራቸዉ፡፡ ከዚህም ጋር በተያያዘ አብዛኛዎቹ ቦታዎች ላይ የተለያየ መጠን ለዉ ዝናብ የተመዘገበ ሲሆን፤ በመካከለኛዉና ምስራቅ ኢትዮጵያ አካባቢዎች ላይም አነስተኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በመሆኑም በምዕራብ አማራ፣ በቤንሻንጉል፣ በምዕራብና ደቡብ ኦሮሚያ፣ በጋምቤላ፣ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች፣ በሲዳማ፣ በጥቂት የመከከለኛዉና ምስራቅ የሀገራችን አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከkለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ የተመዘገበ ሲሆን፤ በአንዳንድ ቦታዎች ላይም ከባድ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ለመጥቀስም በጎሬ 43.0፣ በአርጆ 34.2፣ በጋትራ 30.2፣ በማሻ 30.4፣ በጨዋቃ 36.0፣ በቡሬ  52.7፣  39.2፣ 46.2ና 36.5፣ በአይራ 55.2፣ በነቀምቴ 43.5፣ በጊምቢ 44.1፣  በአልጌ 31.0ና 40.0፣ በጅማ 34.6፣ በማጂ 33.5፣ በአማን 38.6ና 33.8፣ በቴፒ 43.7፣ በዲላ 43.4፣ በሳዉላ 41.0፣ በአቦቦ 44.6ና 50.0፣ በላሬ 38.0ና 32.3፣ በጋምቤላ 43.1 እና በፉኝዶ 34.5፣ በሚሜ ይገኙበታል፡፡  በሌላ በኩል በሀገሪቱ ቆላማ ቦታዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ ሙቀት ካለፉት ወራት አንፃር ጨምሮ የተስተዋለ ከመሆኑም ባሻገር በአንዳንድ ስፍራዎች ላይ እስከ 45 ዲግሪ ሴልሽየስ ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ለመጥቀስም በሰመራ 44.6፣ በዱብቲ 43.5፣ በኤሊዳር 42.6፣ በአይሻ 43.0፣ በአዋሽ አርባ 42.5፣ በመተሃራ 41.0፣ በጋምቤላ 43.1፣ በመተማ 41.2፣ በጎዴ 39.2፣ በቀብሪደሃር 39.6፣ በድሬዳዋ 39.6 እና በላሬ 38.0  በዲግሪ ሴልሽየስ ይገኙበታል፡፡


ባለፈዉ የሜይ ወር የዘነበዉ ዝናብ ከቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም በሁሉም የወለጋ ዞኖች፣ በኢሉ አባቦራ፣ በቡኖ በደሌ፣ በጅማ፣ በባሌ፣ በምዕራብ አርሲ፣ በጥቂት የጉጂና ቦረና፣ በሲዳማ፣ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች፣ በደቡብ ምዕራብ እና ጋምቤላ ክልሎች ሁሉም ዞኖች፣ በማኦ ኮሞ ልዩ ወረዳ፣ በጥቂት የከመሽና መተከል ዞኖች ላይ ከ50-362 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ7-25 ቀናት ያህል ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን፤ በአብዛኛዎቹ የቦረናና ጉጂ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ፣ ምዕራብና ደቡብ ምዕራብ ሸዋ፣ በምዕራብ፣ መካከለኛዉና ደቡብ ጎንደር፣ በምዕራብና ምስራቅ ጎጃም ዞኖች ላይ ከ25-50 ሚሜ የሚደርስ ዝናብ ከ7 ላነሱ ቀናት ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 6 እና 7) ፡፡

ባለፈዉ የሜይ ወር የዘነበዉ ዝናብ ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር በጋምቤላ እና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልሎች ሁሉም ዞኖች፣ በሁሉም የወለጋ ዞኖች፣ በቡኖ በደሌ፣ በኢሉ አባቦራ እና ጅማ፣ በማኦ ኮሞ ልዩ ወረዳ፣ በጥቂት የከመሽ፣ በደቡብ ኦሞ እና በጎፋ ዞኖች ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን፤ የተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ከመደበኛው ያነሰ የዝናብ መጠን ነበራቸው (ካርታ 8) ፡፡


ካርታ 6   ኢ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 7 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት



ካርታ 8 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር





ከመደበኛ በታች መደበኛ ከመደበኛ በላይ

# እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2022 የነበረው የአየር ጠባይ በእርሻ ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፈው የሜይ ወር 2022 ለወቅቱ ዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታን የሚፈጥሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ እና በምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተሻለ ገፅታ ነበራቸዉ ከዚህም ጋር በተያዘ በአብዛኛዎቹ ቦታዎች ላይ የእርጥበት ስርጭቱ ብዙ ቦታዎችን ያዳረሰ የነበር ሲሆን፤ በመካከለኛዉና ምስራቅ ኢትዮጵያ አካባቢዎች ላይም አነስተኛ መጠን ያለዉ እርጥበት አግኝተዋል፡፡ ይህም ሁኔታ በበልግ አብቃይ እና ተጠቃሚ የሀገሪቱ ክፍሎች ተዘርተው ፍሬ በማፍራት እና  በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የበልግ ሰብሎች ቀጣይ እድገታቸው ላይ ጠቀሜታ የነበረው ሲሆን፤ እንዲሁም ለረጅም ጊዜ ሰብሎች የማሳ ዝግጅትና ለዘር እርሻ እንቅስቃሴ፣ ለቋሚ ሰብሎች የውሀ ፍላጎት መሟላት በተጨማሪም ለአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለግጦሽ ሳር እና ለመጠጥ ዉሃ አቅርቦት አመቺ ሁኔታን የፈጠረ ነበር፡፡ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ አልፎ አልፎ የነበረው ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ለአብዛኛው የእርሻ እንቅስቃሴ ጠቀሜታው የጎላ የነበረ ቢሆንም፤ በተወሰኑ ቦታዎች ላይ አሉታዊ ጎን ነበረዉ፡ ፡ በተጨማሪም በመካከለኛው፣ በምስራቅ አማራና በደቡብ ትግራይ በልግ አብቃይ አካባቢዎች ላይ የእርጥበት መቀነስ የነበረ ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ ለበልግ ሰበሎች እድገት በመጠኑም ቢሆን አሉታዊ ጎን ነበረዉ፡፡ በሌላ በኩል በሀገሪቱ ቆላማ ቦታዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ ሙቀት ካለፉት ወራት አንፃር ጨምሮ የተስተዋለ ከመሆኑም ባሻገር በአንዳንድ ስፍራዎች ላይ እስከ 45 ዲግሪ ሴልሽየስ ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ይህም የተስተዋለው ከፍተኛ ሙቀት ከነበረው የዝናብ እጥረት ጋር ተያይዞ በእርሻው እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ጎን ነበረው (ካርታ 9)፡፡


ካርታ 9   እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# ኢ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2022 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ከሜይ1-31/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ በተመለከተ በአብዛኛው ባሮአኮቦ፣ ኦሞጊቤ፣ የመካከለኛውና የታችኛው ስምጥሸለቆ፣ የላይኛው ገናሌዳዋ እንዲሁም የታችኛው አባይ ተፋሰሶች ላይ የተሻለ እርጥበት ሁኔታ የተስተዋለባቸው ናቸው፡፡ በአብዛኛው ገናሌዳዋ እና በጥቂት የመካከለኛው አባይ ተፋሰሶች ላይ ደግሞ መጠነኛ እርጥበት ሁኔታ እንደነበራቸው ተስተውሏል፡፡ በተቀሩት ተፋሰሶች ላይ ደረቅ እና ከፊል ደረቅ ሁኔታ አመዝኖ እንደነበር ተስተውሏል (ካርታ 10) ፡፡

ካርታ 10 ኢ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2022 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ

በመደበኛው ሁኔታ ወቅታዊው የክረምት ዝናብ ቀደም ብሎ በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚጀምር ሲሆን፤ በሂደትም እየተጠናከሩ ከሚሄዱ የክረምት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ጋር ተያይዞ በጁን ወር የተቀሩትን የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን ያዳርሳል፡፡

` በመጪው የጁን ወር ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለያዩ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ላይ አንጻራዊ ጥንካሬ ሊያሳዩ እንደሚችሉና በተለይም በደቡብ ምዕራብ እና በመካከለኛዉ የሃገሪቱ ቦታዎች ላይ ዝናቡ በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተሻለ ሊሆን እንደሚችልና ከጁን አጋማሽ በኂላ ዝናቡ ቀስ በቀስ ወደ ምዕራብና ሰሜን ምዕራብ አከባቢዎች ላይ ሊስፋፉ እንደሚችል የሚጠበቅ ሲሆን፤ በአንዳንድ አካባቢዎችም ላይ አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩ ደመናዎች ነጎድጓድማና ከባድ ዝናብ ሊኖር እንደሚች የትንበያ መረጃዎች ይጠቅማሉ፡፡

በአጠቃላይ በሚቀጥለው የጁን ወር ከኦሮሚያ ክልል ሁሉም የወለጋና የሸዋ ዞኖች፤ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ አርሲና ምዕራብ አረሲ፤ ከአማራ ክልል ምዕራብና ምሥራቅ ጎጃም፣ አዊ ዞን፣ የሰሜን፣ የመካከለኛዉ፣ የምዕራብና የደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ የባህር ዳር ዙሪያ፣የዋግህምራ፤ ከትግራይ ክልል የምዕራብና የሰሜን ምዕራብ ዞኖች፤ የጋምቤላና የቤንሻንጉል ዞኖች በተጨማሪም የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል አብዛኛው ዞኖች፣ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያና የሲዳማ ዞኖች ከመደበኛው ጋር የተቀራረበና አልፎ አልፎም በአንዳንድ ቦታዎቻቸው ላይም ከመደበኛ በላይ ዝናብ ያገኛሉ። በተጨማሪም ሊጠናከሩ እንደሚችሉ ከሚጠበቁ የደመና ክምችቶች በጥቂት የደቡብምዕራብ የሃገሪቱ ቦታዎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ይኖራል። በአንጻሩ ከኦሮሚያ የጉጂ፣ ባሌ፣ ምዕራብ እና ምሥራቅ ሐረርጌ፤ ዞኖች፤ ከትግራይ ክልል የመካከለኛዉና የደቡብ ትግራይ ዞኖች በአንዳንድ ቦታዎቻቸው ላይ አነስተኛ መጠን ያለዉ ዝናብ እንደሚያገኙ የሚጠበቅ ሲሆን፤ የተቀሩት የሀገሪቱ ዞኖች ግን ደረቅ ሆነው ይሰነብታሉ።

## እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2022 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ በጁን ወር አብዛኛዎቹ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ከሚኖራቸው ምቹ የእርጥበት ሁኔታ ጋር ተያይዞ በስፋት የማሳ ዝግጅት የሚያከናውኑበት እና የተለያዩ የመኸር ሰብሎችን የሚዘሩበት ወር ነው።

በተሰጠው የጁን ወር የአየር ጠባይ ትንበያ መሠረት በአብዛኛዎቹ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ በተለይም በደቡብ ምዕራብ በመካከለኛዉና በሰሜን ምዕራብ የሃገሪቱ ቦታዎች ላይ ዝናቡ በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተሻለ ሊሆን እንደሚችል ይጠበቃል። ይህም የሚጠበቀው ዝናብ የአፈር ውስጥ እርጥበትን ከማሻሻልም አልፎ ከጁን ጀምሮ የዘር ጊዜና የማሳ ዝግጅት በሚካሄድባቸው አካባቢዎች ወቅቱን በጠበቀ መልኩ ዘር ለመዝራት አመቺ እንደሚሆን የሚጠበቅ ሲሆን፤ ዘግይተው ለተዘሩና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የበልግ ሰብሎች የውኃ ፍላጎታቸውን ከሚሟላት አንፃር አዎንታዊ ሚና የሚኖረው ሲሆን ከኤፕሪል ጀምሮ ቀደም ብለው ለተዘሩ እንደ በቆሎና ማሽላ ለመሳሰሉ የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎች የውኃ ፍላጎታቸውን እንዲያሟሉ የጎላ አስተዋፅዖ እንደሚኖረው ይታመናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአርብቶ አደርና በከፊል የአርብቶ አደር አካባቢዎች እንዲሁም በምስራቅ ሀረርጌ በመካከለኛውና ደብብ ትግራይ አካባቢዎች ላይ የሚጠበቀው እርጥበት አነስተኛ ቢሆንም የማሳ ዝግጅት ለማከናወንም ሆነ ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውኃ አቅርቦት አዎንታዊ አስተዋፅዖ ይኖረዋል፡፡ በሌላ በኩል በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ ሊኖር የሚችለው ከባድ ዝናብ በተለይም በደቡብ ምዕራብ የአገሪቱ አካባቢዎችም ሆነ በተከታታይ ዝናብ በማግኘት ላይ በነበሩ ቦታዎች ላይ የአፈር ውስጥ እርጥበት መብዛት እና በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ለወንዝ መሙላትና ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች ላይ የጎርፍ መከሰት የአፈር መሸርሸርና የመሬት መንሸራተት ሊያስከተል ሰለሚችል አስፈላጊው ጥንቃቄ ከወዲሁ እንዲደረግ ይመከራል። በተጨማሪም በአንዳንድ አካባቢዎች ከእርጥበት መብዛት ጋር የተያያዙ የሰብል በሽታዎችም ሆነ የአረም መስፋፋት እንዳይከሰት አስፈላጊውን ጥንቃቄ ለማድረገ የሚያስችል ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል።

## እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2022 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በውሀው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመጪው የጁን ወር እርጥበት ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለያዩ የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ አንጻራዊ ጥንካሬ ሊያሳዩ እንደሚችሉና በተለይም በደቡብ ምዕራብ እና በመካከለኛዉ የሃገሪቱ ተፋሰሶች ላይ እርጥበት በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተሻለ ሊሆን እንደሚችልና ከጁን አጋማሽ በኃላ የእርጥበት መጠን ቀስ በቀስ ወደ ምዕራብና ሰሜን ምዕራብ ተፋሰሶች ላይ ሊስፋፋ እንደሚች የሚጠበቅ ሲሆን፤ በአንዳንድ ተፋሰሶች ላይ ከፍተኛ የእርጥበት መጠን ሊኖር እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በአብዛኛው ባሮአኮቦ፣ ኦሞጊቤ፣ ስምጥሸለቆ፣ አባይ፣ የመካከለኛውና የታችኛው ተከዜ፣ የላይኛው አዋሽ፣ የላይኛው ገናሌዳዋ እንዲሁም ዋቢሸበሌ ተፋሰሶች ከእርጥበታማ እስከ ከፍተኛ የእርጥበት መጠን የሚያገኙ ሲሆን፤ በጥቂት ተፋሰሶች ላይ ደግሞ በጠም ከፍተኛ የእርትበት መጠን ሊኖራቸው እንደሚችል ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም ሊጠናከሩ እንደሚችሉ ከሚጠበቁ የደመና ክምችቶች በጥቂት ባሮአኮቦ፣ ኦሞጊቤ እንዲሁም የአባይ ተፋሰስ ምዕራባዊ አጋማሽ ተፋሰሶች ላይ ከከፍተኛ እሰከ በጣም ከፍተኛ የእርጠበት መጠን ይኖራል። በሌላ በኩል የታችኛው ገናሌዳዋ፣ የመካከለኛው አዋሽ እና የላይኛውና የመካከላኛው ዋቢሸበሌ ተፋሰሶች በጥቂት ቦታዎቻቸው ላይ አነስተኛ የእርጥበት መጠን እንደሚያገኙ ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም በዚህ ወር የምናገኘውን የውሃ ሃብት ጥቅም ላይ ለማዋል የሚመለከታቸው አካላት መዘጋጀት አስፈላጊ መሆኑን እንጠቁማለን፡፡